እስመ፡ እግዚአብሔር፡ ነበበ፤

እግዚአብሔር ይጥፋ፡ ብሎ፡ አዝዟልና፤

፲፱፤ ወይወርስዎ፡ ሰብአ፡ ናጌብ፡ ለደብረ፡ ኤሳው፤

ሰብአ፡ ሣህል፡ ሰብአ፡ በዳ፡ ሲል፡ ነው፤ በምድረ፡ በዳ፡ ይኖሩ፡ የነበሩ፡ እስራኤል፡ የኤሳውን፡ አገር፡ ይወርሳሉ፤

ወሳፌላ፡ ዘኢሎፍሊ፤

የኢሎፍሊ፡ ክፍል፡ የምትሆን፡ ሳፌላን፡ ይወርሳሉ፤

ወይወርስዎ፡ ለደብረ፡ ኤፍሬም፡ ወለ አሕቃላተ፡ ሰማርያ፤

በኢያሱ፡ ጊዜ፡ የኤፍሬምን፡ ዕፃ፡ የሰማርያን፡ አውራጃ፡ ይወርሳሉ፤

ወብንያም፡ ወገለዓድ፤

የብንያምን፡ የገለዓድን፡ ዕፃ፡ ይወርሳሉ፤

ወበሐውርቲሆሙ፤

አገራቸውን፡ ሁሉ፡ ይወርሳሉ፤

፳፤ ወዛቲ፡ ቀዳሚቶሙ፡ ለደቂቀ፡ እስራኤል፡ በምድረ፡ ከነአን፤

የእስራኤል፡ ልጆች፡ መጀመሪያ፡ በከነዓን፡ ያደረጓት፡ ስልፋቸው፡ ይች፡ ናት፤ አንድም፡ መጀመ ሪያ፡ የተደረገችላቸው፡ ተአም ራት፡ ይች፡ ናት፤

ከመ፡ ሰራፕታ፡ በሐውርተ፡ እስራ ኤል፡ እስከ፡ ኤፍራታ፤

ሰራፕታ፡ የእስራኤል፡ አገር፡ እንደመሆኗ፡ እስከ፡ ኤፍራታ፡ ድረስ፡ ይወርሳሉ፤ አንድም፡ እምሰራጵታ፡ እስከ፡ ኤፍራታ፡ ሲል ነው፤ ከሰራጵታ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ኤፍራታ፡ ድረስ፡ ይወርሳሉ፤

ወይወርሱ፡ አህጉረ፡ ናጌብ፤

አህጉረ፡ ሣህል፡ ሲል፡ ነው፤ ይቅርታ፡ የሚደረግበትን፡ አገር፡ ይወርሳሉ፤

፳፩፤ ወእለ፡ ድኅኑ፡ የዓርጉ፡ እም ደብረ፡ ጽዮን፡ ከመ፡ ይትበቀልዎ፡ ለደ ብረ፡ ኤሳው፤

ከባቢሎን፡ የዳኑ፡ እስራኤል፡ የኤሳውን፡ አገር፡ ያጠፉ፡ ዘንድ፡ ከደብረ፡ ጽዮን፡ ይወጣሉ፤

ወይከውን፡ መንግሥት፡ ለእግዚ አብሔር፤

የእግዚአብሔር፡ መንግሥቱ፡ በሚጠት፡ ይገለጣል፤ ትርጓ ሜው፡ እንዳለፈው ነው፡

ተፈጸመ፡ ዘአብድዩ፡ ነቢይ፤

አብድዩ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ደረሰ፡ ተፈጸመ፤

በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ ምስሌነ፡ ወስ ብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡

አነቃቅቶ፡ ለአስጀመረን፤ አተ ጋግቶ፡ ላስፈጸመን፡ ለእግዚ አብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግ ባው፤ አሜን፡ በውነት፡፡

የግል ቤተ መጻሕፍት

# ዘዮናስ ነቢይ

## መቅድም፤

ዮናስ፡ ማለት፡ ርግብ፡ ማለት፡ ነው፤ ጌታ፡ ተነሥተህ፡ ወደ ነነዌ፡ ሂድ፡ አለው፤

ወስብከ፡ ሎሙ፤

ነነዌ፡ እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ በእሳት፡ ትጠፋለች፡ ብለህ፡ አስተምራቸው፤ ክፋታ ቸው፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ ደርሷልና፤ ዮናስም፡ አንተ፡ መሐሪ፡ ወመ ስተሣህል፡ ነህ፤ እሳት፡ መው ረዱ፡ የቀረ፡ እንደሆነ፡ ነቢየ፡ ሐሰት፡ እባል፡ የለም? ብሎ፡ ዝም አለ፤ ሂድ፡ ብልህ፡ ብሎ፡ ጌታ፡ ገሥጸው፤ ዮናስ፡ ማለት፡ የዋህ፡ ማለት፡ ነውና፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ከፊቱ፡ ቢያገኘኝ፡ አይደለም? ብሎ፤ ወተኃጥዐ፡ እምገጸ፡ እግዚአብሔር፡ እን ዲል፤ ከእግዚአብሔር፡ ፊት፡ የሸሸሁ፡ መስሎት፡ ሄደ፤

ወረከበ፡ ሐመረ፡ ዘይነግድ፤

ወደ፡ ኢዮጴ፡ የሚሄድ፡ መር ከብ፡ አገኘ፤ መርከቡን፡ ተወጃ ጅቶ፡ ወጥቶ ተቀመጠ፤ እግዚ አብሔርም፡ ጽኑ፡ ነፋስ፡ አስ ነሣ፡ ማዕበሉም፡ ሞገዱም ተነሣ፤ መርከቡም፡ ይሰበር፡ ዘንድ፡ ስርግርግ፡ አለ፤ መር ከቡ፡ የቀለለን መስሏቸው፡ ገንዘባቸውን፡ ከባሕር፡ ላይ፡ ይጥሉ፡ ጀመር፡ ያን፡ ጊዜ፡ ዮናስ፡ በከርሠ፡ ሐመሩ፡ ውስጥ፡ ተኝቶ፡ ያንኮራፋ፡ ነበር፤ ቀዛ ፊው፡ ወርዶ፡ ዮናስን፡ ታድ ነን፡ ዘንድ፡ ተነሥ፡ የፈጣሪ ህን፡ ስም ጥራ፡ አለው፤ ይህ፡ የመጣባችሁ፡ መከራ፡ በኔ፡ ምክንያት፡ ነውና፡ እኔን፡ አን ሥታችሁ፡ ጣሉኝ፡ አላቸው፤

ምንት፡ ተግባርከ፤

ማንን፡ ታመልካለህ? አገር ህስ፡ ወዴት፡ ነው? ወገኖች ህስ፡ እነማናቸው፡ አሉት፤ በወገኔም፡ ዕብራዊ፡ ነኝ፤ አይቴ፡ ብሔርከ፡ ሳሉት፡ አይመል ስም፡ የማመልከውም፡ ሰማ ይን፤ ምድርን፤ ባሕሩን፤ የብ ሱን፡ የፈጠረ፡ ነው፡ አላቸው፤ ይህን፡ ቢላቸው፡ እጅግ፡ ፈሩ፡ አንስተን፡ የጣልነው፡ እንደሆ ነማ፡ ዕዳ፡ ይሆንብን፡ የለም? ብለው፡ እጣ፡ ተጣጣሉ፤ ወወ ረደ፡ ዕፃ፡ ላዕለ፡ ዮናስ፡ እን ዲል፤ በዮናስ፡ ዕጣ፡ ወጣበት፡

www.ethiopianorthodox.org

ወረደ፡ ማለቱ፡ ግን፡ በራሳ
ቸው፡ ላይ፡ ሰብቀው፡ ይጥሉ
ታልና፡ ዕዳ፡ አታድርግብን፡
ብለው፡ አንስተው፡ ከባሕር፡
ላይ ጣሉት፤ የታዘዘ፡ ዓሣ፡
አንበሪ፡ ተቀብሎ፡ ዋጠው፡
ባሕርም፡ ድርጎዋን፡ ተቀብላ፡
ጸጥ፡ አለች፤ በሦስተኛው፡ ቀን፡
በአንቀጸ፡ ነነዌ፡ ወስዶ፡ ተፋው፤
ዮናስ፡ ይች፡ አገር፡ ማን፡ ትባ
ላለች? ብሎ፡ ጠየቀ፤ ነነዌ፡
ትባላለች፡ አሉት ያ፡ ያለኝ፡
ነገር፡ ደረሰ፡ ብሎ፡ እስከ፡
ሠሉስ፡ ዕለት፡ ትትገፈታዕ፡
ነነዌ፡ እያለ፡ ያስተምር፡ ጀመረ፤
ንጉሡ፡ ስልምናሶር፡ ነው፤
ልጅ፡ ከናቱ፤ ላም፡ ከጥጃዋ፡
አትገናኝ፤ ወደ፡ ስምሪትም፡
አይሂዱ፡ ብሎ፡ አዋጅ፡ ነገረ፤
ሰዎችም፡ ምንጣፍ፡ ለብሰው፡
ትቢያ፡ ነስንሰው፡ ንስሐ፡ ገቡ፤
እግዚአብሔርም፡ አዘነላቸው፤
ዮናስ፡ እሳት፡ ባለመውረዱ፡
አዘነ፡ ጥንቱንስ፡ በሀገሬ፡ ሳለሁ፡
ተናግሬ፡ የለም፤ ነቢየ፡ ሐሰት፡
ተብሎ፡ ከመኖር፡ መሞት፡
ይሻለኛል፡ አለ፤ ጌታም፡ ዮናስ፡
እሳት፡ ባለመውረዱ፡ አዘንህ?
አለው፤ እሱም፡ አዎን፡ አለው፤

እንዲህ፡ ቢለው፡ ወዲያው፡
እሳት፡ የሚወርድ፡ መስሎት፡
ከከተማው፡ ወደውጭ ወጥቶ፡
ጎጆ፡ ሠርቶ፡ ተቀመጠ፤ ኋላ፡
እግዚአብሔር፡ ዋዕየ፡ ፀሐይ፡
ራሱን፡ እንዳይመታው፡ ቅል፡
በቅላ፡ ጎጆውን፡ ትሸፍንለት፡
ዘንድ፡ አዘዘ፤ እሱም፡ ደስ፡
አለው፤ ተመልሶ፡ ተኛ፡ በማ
ግስቱ፡ የታዘዘ፡ ትል፡ ቆርጦ፡
ጣላት፡ ደረቀች፤ ዋዕየ፡ ፀሐይ፡
ራሱን፡ መታው፤ አዳጊት፡ የሚ
ባል፡ ራስ፡ ፍልጠት፡ (ምታት)
ነበረበትና፡ ተነሣበት፤ አሁን፡
ይህን፡ ገንዘብ፡ ብለኸው፡ ነው?
ብሎ፡ አዘነ፤ ጌታም፡ ጥቀኑ፡
ኃዘንከ፡ በእንተ፡ ሐምሐም፡ ዘሌ
ሊተ፡ በቈለት፡ ወሌሊተ፡ ማለ
ነት፤ ባልተከልሃት፤ ባልደከ
ምህባት፤ ውሀ፡ ባላጠጣሃት፤
ሌሊት፡ በቅላ፡ ሌሊት፡ በጠፋች፡
ቅል፡ እጅግ፡ አዘንህ? አለው፤
አዎን፡ አለው፤
እኔስ፡ ከዐሥራ፡ ሁለት፡ ዕልፍ፡
የሚበዙ፡ ከዐሥራ ሦስት፡
ዕልፍ፡ ...



ብለው፡ የሚወረውሩ፡ ኃያላን፡
ላሉባት፡ ለነነዌ፡ ላዘንላት፡
ልራራላት፡ አይገባምን አለው፤
አዎን፡ ይገባሃል፡ ብሎ፡ ራሱን
አስፈርዶ፡ አድኗታል፤ ነገዱ፡
ከነገደ፡ ይሳኮር፡ ነው፤ አባቱ፡
አማቴ፡ እናቱ፡ ሶና፡ ይባላሉ።

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡
ኀበ፡ ዮናስ፡ ወልደ፡ አማቴ፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤
ከአማቴ፡ ልጅ፡ ከዮናስ፡ ዘንድ፡
የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብ
ሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤
ይህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ሠለስቱ፡
ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡ አርእስት፡
ሲሰጡ፡ አርእስት፡ ሰጥተው
ታል፤ እርሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡
ወይቤሎ፡ ተንሥእ፡ ብሎ፡
ያመጣዋል፤

፪፤ ወይቤሎ፡ ተንሥእ፡ ወሑር፡
ኀበ፡ ነነዌ፡ ሀገር፡ ዓባይ፡ ወስብክ፡
ሎሙ፤

ደግ፡ ሀገር፡ ወደምትሆን፡ ወደ
... አለው፤

እስመ፡ ዓርገ፡ እክዮሙ፡ ኀቤየ፤

ድኃ፡ መበደላቸው፡ ከኔ፡ ዘንድ፡
ደርሷልና፤ አንድም፡ ከቤተ፡
ጣዖት፡ ገብተው፡ ስምዓኒ፡
በዓል፤ ስምዓኒ፡ በዓል፡ እያሉ፡
መጮሃቸው፡ በዝቷልና፤

፫፤ ወሖረ፡ ዮናስ፡ ወተኃጥአ፡
ብሔረ፡ ተርሴስ፡ እምገጸ፡ እግዚ
አብሔር፤

ዮናስ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡
የታጣሁ፡ መስሎት፡ ይህ፡
ሁሉ፡ ከፊቱ፡ ቢያገኘኝ፡ አይደ
ለም፡ ብሎ፡ ደሴት፡ ወደአለው፡
ባሕር፡ ሄደ፤

ወወረደ፡ ዮናስ፡ ሀገረ፡ ኢዮጴ፤

ኢዮጴ፡ የሀገር፡ ስም፡ ነው፤
ባሕር፡ ወደ፡ አለባት፡ ሀገር፡
ሄደ፤

ወረከበ፡ ሐመረ፡ ዘይነግድ፡ ብሔረ፡
ተርሴስ፤

ደሴት፡ ወደአለው፡ ባሕር፡
የሚሄድ፡ መርከብ፡ አገኘ፤

ወተአሰበ፡ ሐመረ፡ በንዋዩ፤

በገንዘቡ፡ መርከቡን፡ ተስ
ማምቶ፤

ወዓርገ፡ ውስቴቱ፤

ወጥቶ፡ ተቀመጠ፤

ከመ፡ ይንግድ፡ ምስሌሆሙ፡ ተርሴስ፤

ከነዚያ፡ ጋራ፡ ወደ፡ ደሴቱ፡
ይሄድ፡ ዘንድ፤

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ወተኀጥአ፡ እምገጸ፡ እግዚአብሔር፤

ከእግዚአብሔር፡ ፊት፡ የታጣሁ፡ መስሎት፡ ኮብልሎ፡ ሄደ፤

፬፤ ወአምጽአ፡ እግዚአብሔር፡ ነፋስ፡ ዓቢየ፡ ውስተ፡ ባሕር፤

እግዚአብሔር፡ በባሕር፡ ጽኑ፡ ነፋስ፡ አስነሣ፤

ወዓብየ፡ ማዕበለ፡ ባሕር፤

ማዕበሉ፤ ሞገዱ፡ ከፍ፡ ከፍ አለ፤

ወተመንደበ፡ ሐመሮሙ፡ እስከ፡ ይሰበር፤

እስኪሰበር፡ ድረስ፡ መርከቡ፡ ስርግርግ፡ አለ፤

፭፤ ወፈርሁ፡ ኖትያት፤

ቋትለኞች፡ እንስጥማለን፡ ብለው፡ ፈሩ፤

ወአውየዉ፡ ኵሎሙ፡ ኀበ፡ አማል ክቲሆሙ፤

ሁሉም፡ ወደጣዖታቸው፡ ጮሁ፤

ወአስተዋፅዑ፡ ወገደፉ፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ንዋዮሙ፡ ከመ፡ ይቅልል፡ ሐመሮሙ፤

መርከባቸው፡ ይቀልላቸው፡ ዘንድ፡ ገንዘባቸውን፡ እያወ ጣጡ፡ ከባሕር፡ ላይ ጣሉ፤

ወወረደ፡ ዮናስ፡ ውስተ፡ ከርሠ፡ ሐመር፡ ወኖመ፡ ወንኀረ፤

ዮናስ፡ ወደከርሠ፡ ሐመሩ፡ ወርዶ፡ ተኝቶ፡ ያንኮራፋ፡ ነበር፤

፮፤ ወመረደ፡ ኀቤሁ፡ ዘይሔድፍ፤

ቋትለኛው፡ ወደሱ፡ ወርዶ፤

ወይቤሎ፡ ምንት፡ ያነውመከ፤

ምን፡ ያስተኛሀል፤

ተንሥእ፡ ወጸውዕ፡ ስመ፡ አምላክከ፡ ከመ፡ ያድኅነነ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ያድነን፡ ዘንድ፡ ተነሥተህ፡ የፈጣሪህን፡ ስም፡ ጥራ፤

ወኢንመውት፤

አንሙት፡ አለው፤

፯፤ ወተባሀሉ፡ በበይናቲሆሙ፡ ንዑ፡ ንትዓፀው፤

እርስ፡ በርሳቸው፡ ኑ፡ እጣ፡ እን ጣጣል፡ ተባባሉ፤

ወናዕምር፡ በበይነ፡ መኑ፡ ረከበተነ፡ ዛቲ፡ እኪት፤

ይች፡ ያገኘችን፡ መከራ፡ ስለ ማንም፡ እንደሆነች፡ እንወቅ፤

ወተዓፀዉ፡ ዕፃ፤

እጣ፡ ተጣጣሉ፤

ወወረደ፡ ዕፃ፡ ላዕለ፡ ዮናስ፤

በዮናስ፡ ዕጣ፡ ወጣበት፤ ወረደ፡ ማለቱ፡ ግን፡ በራሳቸው፡ ላይ፡ ሰብቀው፡ ይጥሉታልና፤

፰፤ ወይቤልዎ፡ ንግረነ፡ በበይነ፡ መኑ፡ ረከበተነ፡ ዛቲ፡ እኪት፤

ይች፡ ያገኘችን፡ መከራ፡ በማ ንም፡ እ[illegible]፤



ወምንት፡ ተግባርከ፤

ማንን፡ ታመልካለህ፤

እምአይቴ፡ መጻእከ፡ ወአይቴ፡ ተሐውር፤

ከወዴት፡ መጣህ፡ ወዴትስ፡ ትሄዳለህ፤

ወአይቴ፡ ብሔርከ፤

አገርህ፡ ወዴት፡ ነው፤

ወምንት፡ ሕዝብከ፤

ወገኖችህስ፡ እነማን፡ ናቸው፡ አሉት፤

፱፤ ወይቤሎሙ፡ ዮናስ፡ ገብረ፡ እግዚአብሔር አነ፡ ዕብራዊ፤

ምንት፡ ሕዝብከ፡ ላሉት፡ ዕብ ራዊ፡ ነኝ፡ አለ፤

ወአምላኪየ፡ እግዚአብሔር፡ አምላከ፡ ሰማይ፡ ወምድር፤

ምንት፡ ተግባርከ፡ ላሉት፡ ፈጣ ሪዬም፡ ሰማዩን፡ ምድሩን፡ የፈ ጠረ፡ እግዚአብሔር፡ ነው፤

ዘገብረ፡ ባሕረ፡ ወየብሰ፤

የብሱን፡ ባሕሩን፡ የፈጠረ፡ እግ ዚአብሔር፡ ነው፤ አይቴ፡ ብሔ ርከ፡ ላሉት፡ አይመልስም፤

፲፤ ወፈርሁ፡ እሙንቱ፡ ዕደው፡ ዓቢየ፡ ፍርሃተ፤

እንዲህ፡ ቢላቸው፡ እነሱም፡ [illegible] ፈሩ፤

ወይቤልዎ፡ ምንተ፡ ገበርከ፤

ምን፡ አደረግህ፡ አሉት፤

ወአዕመርዎ፡ እሙንቱ፡ ዕደው፡ እስመ፡ ነገሮሙ፡ ከመ፡ እምገጸ፡ እግዚአብ ሔር፡ ተኀጥአ፤

ኮብልሎ፡ እንደመጣ፡ አስቀድሞ፡ ነግሯቸው፡ ነበርና፡ ከእግዚአ ብሔር፡ ፊት፡ ሸሽቶ፡ እንደ ሄደ፡ አወቁ፤

፲፩፤ ወይቤልዎ፡ ምንተ፡ እንከ፡ ንረሲከ፡ ከመ፡ ይኅዳዕ፡ ባሕር፤

ባሕሩ፡ ጸጥ፡ ይልልን፡ ዘንድ፡ ምን፡ እናድርግ፡ አሉ፤

እስመ፡ ይትሐወክ፡ ባሕር፡ ወይት ነሣእ፡ ማዕበል፡ ዓቢይ፤

ባሕሩ፡ ማዕበሉ፡ ፈጽሞ፡ ይነ ሣሣ፡ ነበርና፤

፲፪፤ ወይቤሎሙ፡ ዮናስ፡ ንሥኡኒ፡ ወውርዉኒ፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ወየሐድግ ክሙ፡ ባሕር፤

ዮናስም፡ እኔን፡ አንሥታችሁ፡ ከባሕር፡ ጣሉኝ፤ ባሕሩ፡ ፀጥ፡ ይልላችኋል፡ አላቸው፤

አነ፡ አአምር፡ ከመ፡ በእንቲአየ፡ መጽ አክሙ፡ ዝንቱ፡ ማዕበል፡ ዓቢይ፤

ይህ፡ ጽኑ፡ ማዕበል፡ የተነሣባ ችሁ፡ በኔ፡ ምክንያት፡ እንደ ሆነ፡ እኔ፡ አውቃለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወተበዓሱ፡ ወፈቀዱ፡ ይት
መየጡ፡ መንገለ፡ ምድር፡ እሙንቱ፡
ዕደው፤

እኒህ፡ ሰዎች፡ ወደኋላቸው፡
ይመለሱ፡ ዘንድ፡ ተጣሉ፤
መመለሱን፡ ወደዱ፤

ወስዕኑ፤

መመለስ፡ ተሳናቸው፤

እስመ፡ ይትሀወክ፡ ባሕር፡ ወይትነ
ሣእ፡ ላዕሌሆሙ፡ ማዕበል፤

ባሕሩ፡ ይታወክ፡ ነበርና፡ ማዕ
በሉም፡ ይነሳሣባቸው ነበርና፤

፲፬፤ ወዓውየዉ፡ ኵሎሙ፡ ኀቡረ፡
ኀበ፡ እግዚአብሔር፤

ሁሉም፡ አንድ፡ ሁነው፡ ወደእግ
ዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ለመኑ፤

ወይቤሉ፡ ሐሰ፡ ለከ፡ እግዚኦ፡ ታጥ
ፍዓነ፡ በበይነ፡ ነፍሱ፡ ለዝንቱ፡ ብእሲ፤

በዚህ፡ ሰው፡ ምክንያት፡ ታጠ
ፋን፡ ዘንድ፡ አቤቱ፡ አገባብህ፡
አይደለም፤

ወኢትረሲ፡ ላዕሌነ፡ ደመ፡ ጻድቅ፤

የደጉን፡ ሰው፡ ደም፡ በኛ፡ ላይ፡
አታድርገው፤

እስመ፡ አንተ፡ እግዚኦ፡ ዘከመ፡ ፈቀ
ድከ፡ ገበርከ፤

አቤቱ፡ አንተ፡ እንደወደድህ፡
አድርገሃልና፤

፲፭፤ ወነሥእዎ፡ ለዮናስ፡ ወወረ
ውዎ፡ ውስተ፡ ባሕር፤

ዮናስን፡ አንሥተው፡ ከባሕር፡
ጣሉት፤

ወአርመመት፡ ባሕር፤

ባሕርም፡ ድርጐዋን፡ ተቀብላ፡
ዝም፡ አለች፤

፲፮፤ ወፈርህዎ፡ ለእግዚአብሔር፡
እሙንቱ፡ ዕደው፡ ዓቢየ፡ ፍርሃተ፤

እነዚያም፡ እግዚአብሔርን፡ ፈጽ
መው፡ ፈሩት፤

ወሦዑ፡ ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕተ፡
ወበፅዑ፡ ብፅዓተ፤

ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕቱን፡
ሠዉ፡ ሥእለቱንም፡ ተሳሉ።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወአዘዘ፡ እግዚአብሔር፡ ለአን
በሪ፡ ዓቢይ፡ የኀጦ፡ ለዮናስ፤

ዮናስን ይውጠው፡ ዘንድ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ዓሣ፡ አንበሪውን፡
አዘዘው፤

ወነበረ፡ ዮናስ፡ ውስተ፡ ከርሡ፡ አንበሪ፡
ሠሉሰ፡ መዋዕለ፡ ወሠሉሰ፡ ለያልየ፤

ዮናስ፡ በከርሡ፡ አንበሪ፡ ሦስት፡
መዓልት፡ ሦስት፡ ሌሊት፡
አደረ፤



፪፤ ወጸለየ፡ ዮናስ፡ ውስተ፡ ከርሡ፡
አንበሪ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኩ፤

ዮናስ፡ በከርሡ፡ አንበሪ፡ ሁኖ፡
ከፈጣሪው፡ ከእግዚአብሔር፡
ዘንድ፡ ለመነ፤

፫፤ ወይቤ፡ አውየውኩ፡ በምንዳቤየ፡
ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኪየ፤

በመከራዬ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ እግዚ
አብሔር፡ ለመንሁ፤

ወሰምዓኒ፡ በውስተ፡ ከርሠ፡ ሲኦል፡
ቃለ፡ ጽራኅየ፤

በጥልቁ፡ ባሕር፡ ውስጥ፡ ሳለሁ፡
የልመናዬን፡ ነገር፡ ሰማኝ፤ አን
ድም፡ በከርሡ፡ አንበሪ፡ ሳለሁ፡
ልመናዬን፡ ሰማኝ፤ አንድም፡
ሲያል፡ ባሕር፤ ከርሡ፡ አንበሪ፡
በባሕር፡ ውስጥ፡ ባለ፡ በአን
በሪ፡ ውስጥ፡ ሳለሁ፤

ወሰምዓኒ፡ ቃልየ፤

ነገሬን፡ ሰማኝ፤

፬፤ ወወረውከኒ፡ ውስተ፡ ልበ፡ ቀላየ፡
ባሕር፤

በጥልቁ፡ ባሕር፡ ውስጥ፡ ጣልኸኝ፤
አንድም፡ በከርሡ፡ አንበሪ፡
ጣለኸኝ፤

ወአገቱኒ፡ አፍላግ፤

ውሆች፡ ከበቡኝ፤ ነቢይ፡ ነውና፡
በአፍአ፡ ያለው፡ ውሀ፡ ሲከበው፡
ያያል፤ አንድም፡ በከርሡ፡
አንበሪ፡ ያለው፡ ውሀ፡ ሲከ
[illegible]

ወመጽአ፡ ላዕሌየ፡ ኵሉ፡ ማዕበልከ፡
ወሞገድከ፡ እንተ፡ ላዕሌየ፡ ኃለፈ፤

ማዕበሉ፡ ሞገዱም፡ ወደኔ፡
መጣ፤ በኔ፡ ላይ፡ ሄደ፤ ነቢይ፡
ነውና፡ በአፍአ፡ ያለው፡ ማዕ
በሉ፡ ሞገዱ፡ በላዩ፡ ላይ፡
ሲሄድ፡ ያያል፤ አንድም፡ በከ
ርሡ፡ አንበሪ፡ ያለው፡ ውሀ፡
በላዩ፡ ላይ፡ ሲሄድ፡ ያያል፤

፭፤ ወእቤ፡ ተኀጕልኩኑ፡ እንጋ፡
እምቅድመ፡ አዕይንቲከ፤

ከባለሟልነት፡ እንደወጣሁ፡ ቀረ
ሁን፡ አልሁ፤

ወሀሎኩኑ፡ እርአይ፡ ጽርሐ፡ መቅደስከ፤

ከዚህ፡ ከአንበሪው፡ ሆድ፡
ወጥቼ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ አይ፡
ዘንድ፡ አለኝ፤

### ጉባዔ

፮፤ ወአኀዘኒ፡ማይ፡እስከ፡ነፍስየ፤

ውሀው፡ ሰውነቴን፡ እስከ፡ ማስ
ጠም፡ ደርሶ፡ ሥርግርግ፡ አደ
ረገኝ፤ አንድም፡ ውኀዝ፡ ማይ፡
እስከ፡ ርእስየ፡ ራሴን፡ እስኪ
ያሰጥመኝ፡ ድረስ፡ ውሀው፡
ፈሰሰ፤

ወአገተኒ፡ ቀላይ፡ በታሕቱ፤

ውሀው፡ ከበበኝ፤ ነቢይ፡ ነውና፡
በአፍአ፡ ያለው፡ ውሀ፡ ሲከ
በው፡ ያያል፤ አንድም፡ በከ

www.ethiopianorthodox.org

ርሥ፡ አንበሪ፡ ያለው፡ ውሀ፡ ሲከበው፡ ያያል፤

ናሁ፡ ርእስየ፡ ውስተ፡ ንቃቃተ፡ ደብር፤

እነሆ፡ ራሴ፡ በተከፈለው፡ ተራራ፡ መካከል፡ ነው፤ ነቢይ፡ ነውና፡ በተከፈለው፡ ተራራ፡ መካከል፡ ይዞት፡ ሲሄድ፡ ያያል፤ አንድም፡ ጥንቃቃተ፡ ደብር፡ ይላል፤ ደብር፡ አንበሪ፡ ነው፤ ጥንቃቃት፡ አንጀቱ፡ ጉበቱ፡ ነው፤ ራሴ፡ በአንጀቱ፡ በጉበቱ፡ መካከል፡ አለ፤

ወወረድኩ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ከመ፡ መልሕቅ፡ ታሕተ፤

መልሕቅ፡ በጣሉት፡ ጊዜ፡ ወደታች፡ እንዲወርድ፡ ወደጥልቅ፡ ባሕር፡ ወረድሁ፤

፯፤ ትዕርግ፡ ሕይወትየ፡ ዘእንበለ፡ ሙስና፡ ኀቤከ፡ እግዚኦ፡ አምላኪየ፤

አቤቱ፡ ጌታዬ፡ ሰውነቴ፡ ያለ፡ ጥፋት፡ ካንተ፡ ዘንድ፡ ትድረስ፤

፰፤ ሶበ፡ ሐልቀት፡ ነፍስየ፡ ተዘከርክዎ፡ ለእግዚአብሔር፤

ሰውነቴ፡ በመከራ፡ እለይ፡ እለይ፡ ባለች፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔርን፡ አሰብሁት፤

ትብጻሕ፡ ጸሎትየ፡ ቅድሜከ፡ ጽርሐ፡ መቅደስከ፤

ቅድሜከ፡ ጽርሐ፡ መቅደስከ፡ አንድ፡ ወገን፤ ልመናዬ፡ በፊትህ፡ ወደመመስገኛህ፡ ቦታ፡ ወደጽርሐ፡ አርያም፡ ትድረስልኝ፤

፱፤ እለሰ፡ ዓቀቡ፡ ከንቶ፡ ወሐሠተ፡ ገደፉ፡ ሣህሎሙ፤

ከንቱ፡ ጣዖትን፤ ከንቱ፡ ነገርን፤ ሐሰት፡ ነገርን፤ ሐሰት፡ ጣዖትን፡ የሚመለከቱ፡ ሰዎች፡ ግን ይቅርታቸውን፡ አንተን፡ ተዉ፤ አንድም፡ ከመ፡ ይቅልል፡ ሐመሮሙ፡ እንዲል፡ ገንዘባቸውን፡ ከባሕር፡ ላይ፡ ጣሉ፤ ወኮነት፡ ሣህለ፡ ለዓለም፡ እንዲል፤

፲፤ አንሰ፡ ምስለ፡ ቃለ፡ ስብሐት፡ በተጋንዮ፡ እሠውዕ፡ ለከ፤

እኔስ፡ ከምስጋና፡ ጋር፡ በመገዛት፡ መሥዋዕቱን፡ አቀርብልሃለሁ፤

መጠነ፡ ጸለይኩ፡ በሕይወትየ፡ አዕስዮ፡ ለእግዚአብሔር፤

በሕይወተ፡ ሥጋ፡ ሳለሁ፡ ያመሰገንሁትን፡ ያህል፡ በከርሠ፡ አንበሪ፡ ሳለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፤ አንድም፡ በከርሠ፡ አንበሪ፡ ሳለሁ፡ ያመሰገንሁትን፡ ያህል፡ ከከርሠ፡ አንበሪ፡ ከወጣሁ፡ በኋላ፡ አመሰግነዋለሁ፤

፲፩፤ ወአዘዞ፡ እግዚአብሔር፡ ለውእቱ፡ አንበሪ፡ ያውጽኦ፡ ለዮናስ፡ ውስተ፡ ምድር፤

እግዚአብሔር፡ ዮናስን፡ ውሀ፡ ከሌለበት፡ ቦታ፡ ያወጣው፡ ዘንድ፡ አንበሪን፡ አዘዘው፤



ምሳሌ፡ ነው፤ ዮናስ፡ በከርሠ፡ አንበሪ፡ ሦስት፡ መዓልት፤ ሦስት፡ ሌሊት፡ አድሮ፡ እንደ፡ ወጣ፡ ጌታም፡ ሦስት፡ መዓልት፤ ሦስት፡ ሌሊት፡ በመቃብር፡ የማደሩ፡ ምሳሌ፤ ወበከመ፡ ኀደረ፡ ዮናስ፡ ውስተ፡ ከርሠ፡ አንበሪ፡ ሠሉሰ፡ መዋዕለ፡ ወሠሉሰ፡ ለያልየ፡ ከማሁ፡ ሀለዎ፡ ለወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ይንበር፡ ውስተ፡ ልበ፡ ምድር፡ ሠሉሰ፡ መዋዕለ፡ ወሠሉሰ፡ ለያልየ፡ እንዲል።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዳግመ፡ ኀበ፡ ዮናስ፤

ከዮናስ፡ ዘንድ፡ ዳግመኛ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ መጣ፡ ተነገረ፤

፪፤ ወይቤሎ፡ ተንሥእ፡ ወሑር፡ ነነዌ፡ ሀገር፡ ዓባይ፡ ወስብክ፡ ሎሙ፡ በከመ፡ ቀዲሙ፡ ስብከት፡ ዘእቤለከ፡ አነ፤

ደግ፡ ወደምትሆን፡ ወደ፡ ነነዌ፡ ተነሥተህ፡ ሂድ፤ እኔ፡ አስተምር፡ ብዬ፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ እንደነገርሁህ፡ አስተምራቸው፤

፫፤ ወተንሥአ፡ ዮናስ፡ ወሖረ፡ ነነዌ፡ በከመ፡ ይቤሎ፡ እግዚአብሔር፤

ዮናስም፡ እግዚአብሔር፡ እንዳዘዘው፡ ተነሥቶ፡ ወደነነዌ፡ ሄደ፤

ወነነዌሰ፡ ሀገር፡ ዐባይ፡ ይእቲ፡ ለእግዚአብሔር፤

ነነዌ፡ ግን፡ ለእግዚአብሔር፡ ደግ፡ ሰፊ፡ ሀገር፡ ናት፤

ወምዕዋደ፡ ቅጽራሂ፡ እምአንቀጽ፡ እስከ፡ አንቀጽ፡ መጠነ፡ ምሕዋረ፡ ሠሉስ፡ መዋዕል፡ በእግር፤

ከበር፡ እስከበር፡ ያለው፡ የከተማው፡ ዙሪያ፡ በእግር፡ የሦስት፡ ቀን፡ ጐዳና፡ ይሆን፡ ነበር፤

፬፤ ወአልጺቆ፡ ይባዕ፡ ሀገረ፡ ሰበከ፡ እምሕዋረ፡ አሐቲ፡ ዕለት፤

ወደከተማ፡ ሊገባ፡ በቀረበ፡ ጊዜ፡ ያንድ፡ ቀን፡ ጐዳና፡ ሲቀረው፡ ያስተምር፡ ጀመረ፤

ወይቤ፡ እስከ፡ ሠሉስ፡ መዋዕል፡ ትትገፈታዕ፡ ነነዌ፡

እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ ነነዌ፡ ትጠፋለች፡ አለ፤

፭፤ ወተአመኑ፡ ሰብአ፡ ነነዌ፡ በቃለ፡ እግዚአብሔር፤

የነነዌ፡ ሰዎች፡ እግዚአብሔር፡ የተናገረውን፡ ነገር፡ አመኑ፤

ወሰበኩ፡ ጾመ፤

ጾም፡ እንጹም፡ ብለው፡ አዋጅ፡ ነገሩ፤

ወለብሱ፡ሠቀ፡ንዑሶሙ፡ወዓቢዮሙ፤

ታላቁም፡ ታናሹም፡ ምንጣፍ፡ ለበሱ፤

ወአዕተቱ፡ አልባሲሆሙ፡ ወነበሩ፡ ውስተ፡ ሐመድ፤

ልብሳቸውን፡ ትተው፡ አመድ፡ ነስንሰው፡ ንስሐ፡ ገቡ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮፤ ወሰምዐ፡ ንጉሠ፡ ነነዌ፤

የነነዌ፡ ንጉሥ፡ ይኸን፡ ሰምቶ፡ ንጉሡም፡ ስልምናሶር፡ ነው፤

ወተንሥአ፡ እመንበሩ፡ ወሰብሰ፡ ሰቀ፡ ወአዕተተ፡ አልባሲሁ፤

ከዙፋኑ፡ ወርዶ፡ ምንጣፍ፡ ሰብሶ፤

ወነበረ፡ ውስተ፡ ሐመድ፤

አመድ፡ ነስንሶ፡ ንስሐ፡ ገባ፤

፯፤ ወሰበከ፡ ንጉሠ፡ ነነዌ፡ ለንዑሶሙ፡ ወለዓቢዮሙ፤

የነነዌ፡ ንጉሥ፡ ለታላቁም፡ ለታናሹም፡ አዋጅ፡ ነገረ፤

ወይቤ፡ ሰብእ፡ ወእንስሳ፡ ወአልህምት፡ ወአባግዕ፡ ኢይብልዑ፡ ምንተኒ፡

ሰውና፡ እንስሳ፤ ላምና፡ በግ፡ ከምግብ፡ ይከልከሉ፡ አለ፤

ወኢይትረአዩ፡ ሣዕረ፤

ወደሣር፡ አይሰማሩ፤

ወኢይስተዩ፡ ማየ፤

ውሀ፡ አይጠጡ፡ አለ፤

፰፤ ወይልበሱ፡ ሠቀ፡ ኵሉ፡ ሰብእ፤

ሰዎች፡ ሁሉ፡ ምንጣፍ፡ ይልበሱ፤

ወአውየዉ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ኀቡረ፤

አንድ፡ ሁነው፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ለመኑ፤

ወኃደጉ፡ ኵሎሙ፡ እከየ፡ ምግባሮሙ፤

ሁሉም፡ ክፉ፡ ሥራቸውን፤ ቅሚያን፤ ስርቆትን፡ ተዉ፤

አንድም፡ እንስሳት፡ መሰማሪታቸውን፡ ተዉ፤

ወዓመፃ፡ ዘውስተ፡ እደዊሆሙ፤

በጃቸው፡ የሚሠሩትን፡ ጣያቱን፡ ተዉ፤

፱፤ ወይቤሉ፡ መኑ፡ የአምር፡ እመ፡ ይኔስሕ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ያዝንልን፡ እንደሆነ፡ ማን፡ ያውቃል፡ አሉ፤

ወይመይጥ መቅሠፍተ፡ መዓቱ፤

ፈርዶ፡ ያመጣውን፡ መቅሠፍቱን፡ ይመልስ፡ እንደሆነ፡ ማን፡ ያውቃል፤

ወኢንመውት እንከ፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ አንሞት፡ እንደሆን፡ ማን፡ ያውቃል፡ አሉ፤

፲፤ ወርእየ፡ እግዚአብሔር፡ ምግባሮሙ፡ ከመ፡ ነስሑ፡ እምፍኖቶሙ፡ እኩይ፤

እግዚአብሔር፡ ከክፉ፡ ሥራቸው፡ እንደተመለሱ፡ ሐዘናቸውን፡ ዓይቶ፤

እግዚአብሔርኒ፡ ነስሐ፡ እምነ፡ ዘነበበ፡ እኩየ፡ ላዕሌሆሙ፡ ከመ፡ ይግበር፤

እግዚአብሔርም፡ በእርሳቸው፡ ላይ ያደርገው፡ ዘንድ፡ ከተናገረው፡ ክፉ፡ ነገር፡ ከማድረግ፡ ተመለሰ፤

ወኢገብረ፡ እኩየ፤

ክፉ፡ ነገር፡ አላደረገም፤



## ምዕራፍ ፬

፩፤ ወተከዘ፡ ዮናስ፡ ዓቢየ፡ ትካዘ፡ ወኃዘነ፡ ወጸለየ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኩ፤

ዮናስ፡ ፈጽሞ፡ አዘነ፤ ወደ ፈጣሪው፡ ወደ እግዚአብሔር፡ ለመነ፤

፪፤ ወይቤ፡ እግዚኦ፡ አኮኑ፡ ከመዝ፡ እቤ፡ በብሔርየ፤

አቤቱ፡ በሀገሬ፡ ሳለሁ፡ ተናግሬ፡ የለም?

ወበበይነ፡ ዝንቱ፡ ተኃጣዕኩ፡ ተርሴስ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ኮብልዬ፡ ወደ፡ ደሴት፡ የሄድሁ፡ አይደለምን?

እስመ፡ አአምር፡ ከመ፡ መሐሪ፡ አንተ፡ ወመስተሣህል፡ ርኁቀ፡ መዓት፡ ወብዙኃ፡ ምሕረት፡ ወጻድቅ፤

መሐሪ፡ ይቅር፡ ባይ፡ እንደሆንህ፡ ከመዓት፡ የራቅህ፡ ቸርነትህ፡ የበዛ፡ ቸር፡ እንደሆንህ፡ አውቃለሁና፤

ወትኔስሕ፡ በእንተ፡ እኪት፤

ክፉ፡ ሠርተው፡ ቢመለሱ፡ እንድታዝን፡ አውቃለሁና፤

፫፤ ወይእዜኒ፡ እግዚኦ፡ ንሥኣ፡ ለነፍስየ፡ እምኔየ፤

አሁንም፡ አቤቱ፡ ነፍሴን፡ ከሥጋዬ፡ ለያት፤

እስመ፡ ይኄይሰኒ፡ መዊት፡ እምሐዩው፤

ነቢየ፡ ሐሰት፡ ተብሎ፡ ከመኖር፡ መሞት፡ ይሻለኛል፤

፬፤ ወይቤሎ፡ እግዚአብሔር፡ ለዮናስ፡ ጥቀኑ፡ ትቴክዝ፡ አንተ፤

እግዚአብሔር፡ ዮናስን፡ እሳት፡ ባለመውረዱ፡ ፈጽመህ፡ አዘንህን፡ አለው፤

፭፤ ወእምዝ፡ ወጽአ፡ ዮናስ፡ እምሀገር፡ ወነበረ፡ አንቀጸ፡ ሀገር፤

ዮናስም፡ እሳት፡ የሚወርድ፡ መስሎት፡ከከተማ፡ወጥቶ፡ከውጭ፡ ተቀመጠ፤

ወገብረ፡ ሎቱ፡ ልገተ፡ ወነበረ፡ ታሕተ፡ ጽላሎታ፡ እስከ፡ ይሬኢ፡ ዘይከውን፡ ሀገር፤

አገሩ፡ የሚሆነውን፡ እስኪያይ፡ ድረስ፡ ጎጆ፡ ሠርቶ፡ ተቀመጠ፤

፮፤ ወአዘዘ፡ እግዚአብሔር፡ ሐምሐመ፡ ከመ፡ ይብቍል፡ ወበቈለ፤

እግዚአብሔር፡ ቅል፡ ይብቀል፡ ብሎ፡ አዘዘ፡ በቀለ፤

ወፀለሎ፡ ለዮናስ፡ መልዕልተ፡ ርእሱ፡ ከመ፡ ኢያሕምሞ፡ ፀሐይ፤

የዮናስን፡ ራስ፡ ፀሐይ፡ እንዳያገኘው፡ ጎጆውን፡ ሸፈነለት፤

ወተፈሥሐ፡ ዮናስ፡ ዓቢየ፡ ፍሥሐ፡ በእንተ፡ ሐምሐም፤

ቅል፡ በቅሎ፡ ጎጆውን፡ ስለሸፈነለት፡ ዮናስ፡ ፈጽሞ፡ ደስ፡ አለው፤

፯፤ ወአዘዘ፡ እግዚአብሔር፡ በሳኒታ፡ ዕፄ፡ ወቀተላ፡ ለዛቲ፡ ሐምሐም፡ ወየብሰት፤

በማግሥቱ፡ እግዚአብሔር፡ ትል፡ ቆርጦ፡ ይጥላት፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤

www.ethiopianorthodox.org